# አደረች አራዳ !

የጎንቻው!

ዘገየች አራዳ! 'አደረች አራዳ'!፤
የኛ ሞናሊዛ፤ ተውባ ተጓዳ፤
ስትተሻሽ ኖራ ከካደም ከከዳ፤
ከሸጣት ከገዛት ጠልታ ይሁን ወዳ፤
የኛማ መዲና ብልጭልጭ ወረዳ፤
ተሽብባ ይሁን ወይስ ተሞዳሙዳ፤
ዝሙት ዝምተኛ ቅምጥል ተንጓዳ፤
መሄድ ሲከጅላት መቅረት የምትዳዳ፤
ተሽቅርቅራ ይሆን ወይ በግፍ ተዋርዳ፤
አዲስ ፈቅዳ ይሆን ወይስ ደፍሯት ባንዳ፤
ጥሪ የማትመልስ፤ እማታወላዳ፤
ፈርስ ቀይራ ይሆን ሽፍጣ ከባዳ፤
ወይስ እግር ተውርች በአልቦ ተቀፍዳ፤
አለዚያስ ዘምና ፍቅር እያደራች አራት ኪሎ ጓዳ፤
ሽፍታ እያደለበች ቂራን አሰድዳ፤
ደም እያፈሰሰች ለገዳይ ፍሪዳ፤
በጠዋት አትነሳም ቆይታ አረፋፍዳ፤
ሥጋ ተጫጭኗት ጥሬ ጮማ ሙዳ፤
ሲሻት አገር ጠብሳ በሽታ ታውዳ፤
ልታደረጉተው አመድ፤ጥላሸቱን ለአባወራው እዳ፤
ወይ አትፍም፤ አትበስል ወይ አትከስል ስትዳዳ፤
የሃገር ምድጃዋ የሕዝብ ደመራ ከአፎቱ ተማግዳ፤
**ታሳርረናለች ዙሪያዋን እየጤሰን ዝም ብላ ተጥዳ።**

## ሁሉም ኢትዮጵያዊ በአንድ ላይ ቢያብር ወያኔ የቀን እድሜ አይኖረውም!!!

31.08.16